# የACPS Express 12/9/2022: እስከ ዲሴምበር (Dec.) 21 ቀን 2022 ድረስ-ባለው ጊዜ፣ በጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ ፍለጋው ላይ ያላችሁን አስተያየት አጋሩ

## እስከ ዲሴምበር (Dec.) 21 ቀን 2022 ድረስ-ባለው ጊዜ፣ በጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ ፍለጋው ላይ ያላችሁን አስተያየት አጋሩ



የትምህርት ቤት ስርዓታችንን ሊመራ የሚችል አዲስ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅን የመፈለግ ጠንካራ የፍለጋ-ሂደት ውስጥ መሳተፍን፣ የአሌክሳንድርያ የትምህርት ቤት ቦርድ ጀምሯል። በፍለጋው ሂደት ላይ እንደ አማካሪ-ድርጅት/consultant ሆኖ ተሳትፎውን የጀመረው የ'McPherson & Jacobson, L.L.C Executive Recruitment and Development' ሲሆን፤ ለዚህ-የስራ ድርሻ እጩዎችን የመለየት እና የመለየት ስራን በማካሄድ የትምህርት ቤት ቦርድን ያግዛል።

"በጣም ወደ ጥሩ-ውጤት የሚመራ እርምጃ እያደረግን ወደፊት እየገፋን እና ግልጽና በደንብ-የታሰበበትን ሂደት ቀርጸን - ይህም አዲሱን ጠቅላይ-ስራ አስኪያን ለመስየም የትምህርት ቤት ክፍላችንን/division የሚመራልን ይሆናል፤" ብለዋል የትምህርት ቤት ቦርድ - ሊቀ-መንበር ሜጋን አልደርተን (Meagan L. Alderton)። "ሁልጊዜ ግባችን የሚሆነው፣ ተማሪን-ባገናዘበ እና የመረጃ-ስብስብ ላይ ትኩረት ያድረገ (data-driven)፣ አዎንታዊ የትምህርት ባህልን መጠበቅ እና ማቆየት ነው።"

ይህ ሂደት በስራ-ላይ እየተካሄደ ባለበት ጊዜ፤ ከዚህ በታች በጊዜ-አቀማመጥነት በተቀመጠው መሰረት - ጎን-ለጎን በመሆን፤ ቋሚ የሆነ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅን እስከ ማርች (March) 2023 መጨረሻ ድረስ ለመሾም ያለንን ጠንካራ ግባችንን መገንባት እና አላማችንን-ማሳካት ነው። ይህ የጊዜ-አቀማመጥ (timeline)፤ ከሠራተኞች፣ ቤተሰቦች እና ማህበረሰቡ - ትርጉም-ሰጪ አስተያየቶችን የማግኛ ዕድሎችንም ያካተተ ነው። የACPS ማህበረሰባችንን ሊመራ የሚችል የሚቀጥለውን ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅን በመምረጥ-ስራ ላይ እየተሰማራን ባለንበት-ጊዜ፤ እናንተ-የምትሰጡት አስተያየት (feedback) - የሚበረታታ እና ከግምት-ውስጥ የሚገባ ነው።

በተጨማሪም፤ ያላችሁን አስተያየት - በዳሰሳ-ጥናታችን አማካኝነት፣ ከዲሴምበር (Dec.) 9-21 ቀን 2022፤ እስከ 11:59 p.m. EST ጊዜ-ድረስ እንድትሰጡንም - ጋብዘናችኋል። የዳሰሳ-ጥናቱ ማገናኛዎች (Links)፣ በበርካታ ቋንቋዎች መገኘት ይችላል: እንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ፣ አማርኛ፣ አረብኛ እና ዳሪ።

ፍላጎት-ያላቸው አካላቶች፤ የስራ-ድራሻ ዝርዝር-መግለጫውን (job description) እና የማመልከቻ ሂደቱን መመልከት ይችላሉ። እንደሁልጊዜውም፤ ለጠቅላላው የACPS ማህበረሰባችን ለሚያደርጉት ቀጣይነት ያለው እርዳታ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

**የፍለጋ የጊዜ-አቀማመጥ (Search Timeline):**
**ከዲሴምበር (Dec.) 9-21 ቀን፣ 2022**
የባለድርሻ-አካላት (Stakeholder) የዳሰሳ-ጥናቶች ይጀመራሉ

**ዲሴምበር (Dec.) 14 ቀን እና 15 ቀን፣ 2022**
ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጋር፣ ከማዕከላዊ ቢሮ ሠራተኞች እና የትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ የ'PTAC' ቦርድ አድቫይዘሪ ኮሚቴዎች፣ የከተማው ሠራተኞች እና አመራሮች፣ የማህበረሰብ ቡድኖች እና አመራቶች ጋር ውይይቶች-ይደረጋሉ

**ጃንዋሪ (January) 2023**
የባለድርሻ-አካላት (Stakeholder) ሪፖርት ፖስት-ይደረጋል (posted)

**ፌብሩዋሪ (Feb) 2 ቀን 2023**
የማመልከቻዎች መቀበያ-ጊዜ የሚዘጋበት-ቀን

**ማርች (March) 2023**
የመጨረሻ-ተመራጭ እጩዎች ቃለ-መጠይቅ

**በማርች (March) 2023 መጨረሻ-ላይ**
አዲስ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ (superintendent) መምረጥ

**ጁላይ (July) 1 ቀን 2023**

ቋሚ የስራ-ድርሻው ይጀምራል

## የ'ESSER III' የሕዝብ አስተያየት - በዲሴምበር (Dec.) 11 ቀን 2022 በኦንላይን መጋራት የሚችል እና፣ በዲሴምበር (Dec.) 15 ቀን 2022 - የ'Public Hearing'



የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - እስከ ዲሴምበር (Dec.) 11 ቀን 2022 ድረስ፤ የባለድርሻ-አባል (stakeholder) አስተያየቶችን ለማግኘት - የትምህርት ቤት ክፍሉ/school division፤ የ'pandemic relief funds'ን እንዴት መጠቀም-እንደሚችል አስተያየትን-ይጠይቃል። ACPS፣ በ'American Rescue Plan (ARP) Act Elementary and Secondary School Emergency Relief (ESSER) III የእርዳታ ፕሮግራም' አማካኝነት፣ የገንዘብ እርዳታን አግኝቷል።

የትምህርት ቤት ቦርድ፣ በ'ESSER III' የገንዘብ-ስብስብ አጠቃቀም ላይ - በዲሴምበር (Dec.) 15 ቀን 2022 በሚድረገው የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ላይ - የ'Public Hearing'ን ያዘጋጃል። በዲሴምበር (Dec.) 15 ቀን 2022 በሚድረገው 'Public Hearing' ላይ - የመናገር-ጥያቄን፣ በአካል-ቀርቦ (in person)፣ በዙም(Zoom) አማካኝነት ወይም በጽሁፍ-አስተያየትን የማቅረብ-ጥያቄ፤ እስከ ሮብ ዲሴምበር (Dec.) 14 ቀን 2022, ድረስ - የ'Public Hearing' መመዝገቢያ/sign-up ቅጽ'ን በመጠቀም መግባት-አለበት።

የ'ARP ESSER III Fund' ዓላማ፣ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንደገና ለመክፈት እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት ቤት ክንውኖችን ማከናወንን ለመቀጠል፣ COVID-19 በሃገሪቱ ተማሪዎች ላይ ያደረሰውን፣ የቀለም ትምህርት፣ የማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና የአዕምሮ-ጤና ፍላጎቶች ላይ ለተከሰቱት ተጽዕኖዎች ምላሽ መስጠት ላይ ለመርዳት ነው።

ይህ እርዳታ፣ COVID-19 ባስከተለው ተጽዕኖ ምክንያት የትምህርት ቤት ህንፃዎች በመዘጋታቸው፣ በተማሪዎች አገልግሎቶች ላይ ምላሽ ለመስጠት የገንዘብ እርዳታ ይሰጣል። ወደ መደበኛው የትምህርት ቤት ክንውኖችም ለመመለስ፣ ዕቅዶችን ለመቅረጽ እና ለማስፈጸምም፣ የገንዘብ እርዳታው ይውላል። ስለ ACPS የፌደራል የፓንዳሚክ ግራንት (federal pandemic grants) የገንዘብ ሪፖርቶች - የበለጠ መረጃዎችን በ'ACPS' ድህረ-ገጽ ተመልከቱ።

ለዚህ ሂደት አንዱ አካል አድርጎ፤ ማህበረሰባችን እርዳታው - እንዴት ተማሪዎችን፣ ሠራተኛን እና የትምህርት ቤት ክንውኖችን ላይ ጥቅም ላይ ሲውል ለማየት እንደሚፈልጉ ለመረዳት፤ የባለድርሻ አባላት (stakeholder) ግብዓት (input)ን ACPS ይጠይቃል። የACPS ማህበረሰብ አባላቶች፤ ያላቸውን አስተያየት የኦንላይን ግብረ-መልስ (feedback) ቅጽን በመጠቀም፤ ይህም ጥቂት-ደቂቃዎችን ብቻ ለማጠናቀቅ የሚወስድ እና እስከ ዲሴምበር (Dec.) 11 ቀን 2022 ድረስ፤ በእንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ፣ አማርኛ፣ ዳሪ እና አረብኛ መገኘት-በሚችለው ላይ ማስገባት ይችላሉ።

## የዲሴምበር (December) - በአጋርነት እና በጎ-ፍቃደኝነት (Partner & Volunteer) ላይ የሚታዩ-ጉልህ ነገሮች: 'Building Momentum'



'Building Momentum' አገልግሎት-በማይሰጡ፣ ቬተራን-ባለቤትነት ያለው አነስተና የንግድ-ድርጅት (veteran-owned small business) ሲሆን፤ ከአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ጋር ቁልፍ-የሆነ የማህበረሰ አጋር በመሆን፤ ለACPS ተማሪዎች - በመማሪያክፍል ውስጥ ያሉ ጽንሰ-ሃሳቦችን ከእውነተኛው ዓለም አስቸጋሪና ፈታኝ-ነገሮች ጋር በማገናኘት ለመመልከት የሚያበረታታቸው ነው። ካምፖቹ፣ ክፍሎቹ እና የመስክ-ጉዞዎቹ (field trips)፤ ተማሪዎች ሊማሩበት እና ሊገነቡት ከሚችሉት ክልሎች በተጨማሪ ለመግፋት እንዲችሉ ኃይል በመስጠት ይረዳቸዋል። "አጠቃላይ የክፍሎቻችን የመጨረሻ-ግባቸው፤ ለመገንዘብ-ቀላል እንዲሆን ማድረግ እና በእነርሱ ክልል ውጪ ነው ብሎ አንድ ሰው የሚሰማውን - መሣሪያዎችን እና ቴክኖሎጂዎችን - መገኘት-እንዲችሉ ማድረግ ነው፤" ብለዋል የ'Creative Officer' ሹም - አለን ብሩክስ (Allen Brooks)።

ማስተማሩ፤ በኤሌክትሮኒክስ፣ በብረት-ስራ፣ በሮቦት-ስራ እና የእንጨት-ስራ ላይ፤ ከስራ-መስክ ጋር ለተማሪዎች ፍለጋ-የሚያገናኝ ዕድሎችን ዙሪያ በተገነባ ስልጠና ላይ ትኩረት ያደረገ ማስተማር ነው። "ከ'Building Momentum' Innovation Academy ጋር ያለን አጋርነት፤ ልዩ የሆነ ዕድልን ለተማሪዎች - አስደሳች የመገኘት-ስፋት ባላው የቴክኖሎጂ ማስተማር ላይ - የ3D ህትመትን፣ ሌዘር መቁረጫ (laser cutting)፣ ድሮውንስ (drones)፣ ሮቦት-ስራ፣ ኤሌክትሮኒክስ እና ሌሎች-ተጨማሪዎችን ባካተተው-ውስጥ ተማሪዎችን ማሳተፍ ነው፤" የACPS - የ'STEM' አስተባባሪ እና የመጀመሪያ ደረጃ የሂሳብ የትምህርት አሰጣጥ ባለሞያ የሆኑት- ጁሊያ ንውፈር (Julia Neufer) አስተያየታቸውን-ሰጥተዋል። በተጨማሪም ሲገልጹ፤ በእነዚህ ተሞክሮዎች አማካኝነት፣ ተማሪዎች በበርካታ ልዩ መሣሪያዎች ላይ ለመጠቀም እውቀት-ያካበቱ፣ እና ከሁሉ-በበለጠ ሁኔታ ደግሞ - "ተማሪዎች በጥልቀት-የማሰብ ችሎታቸውን፣ ችግሮችን መፍታት፣ የትብብር እና የፈጠራ-ችሎታቸውን በማዳበር ማሳደግ-ችለዋል።" ብሩክስ (Brooks) እንዳስቀመጡት፤ "የችሎታ-ስብስብን ብቻ ከማስተማር ይልቅ፤ ችግርን-የሚፈታ አስተሳሰብን መገንባት የበለጠ-ጠቃሚነት አለው።"

በነዚህ ካምፖች እና ክፍሎች አማካኝነት፤ ለተማሪዎች መማር - ሙከራ-የማድረጊያ እና ፈጠራን የማዳበሪያ እና የማቅረቢያ ዕድሎችን በሚሰጥ አካባቢው ውስጥ እንዲገቡ ዕድሎችን-አመቻችቶ - 'Building Momentum' ፈጥሮላቸዋል። ብሩክስ (Brooks)

እንደሚያምኑበት፤ “ከእኛ ትምህርት ሰጪዎች - ለመበየድ ወይም ብረትን ለማጠፍ - እምነት፣ ልበ-ሙሉነት እና ፈቃድን ሲሰጣቸው፣ እና በሰው-ልጅ ጉልበት የተሰራ የ‘go-kart’ን በመኪና-ማቆሚያው ውስጥ እንዲሄድ በካምፑ-መጨረሻ ላይ ለማድረግ ሲችሉ-መመልከት፤ በጣም አስደሳች-ነው።” በኢኖቬሽን አካዳሚ/Innovation Academy የሚሰጡት ክፍሎች፤ ተማሪዎች ተመቻችተው ከተቀመጡበት ቦታ እንዲወጡ የሚረዳ ነው ብለው ያምናሉ፤ “አንድ-ልጅ ይሰራዋል ብሎ የማይገምተውን ነገር ሰርቶ ከማጠናቀቅ በላይ ምንም ኃይልና-ጉልበት የሚሰጥ ነገር የለም።” ከመስክ-ጉዞው አስቀድሞ፤ የ‘Building Momentum’ ሠራተኛ - ከክፍሉ አስተማሪዎች ጋር በመሆን በተሞክሮው ጊዜ የሚሸፈነው-ትምህርት ከቨርጅኒያ ‘Standards of Learning’ ጋር አብሮ-ጎን ለጎን መሄዱን ለማረጋገጥ-አብረው ይሠራሉ። “እኛ አስተማሪዎች መረዳታቸው ማረጋገጥ እንጂ፣ ስራቸውን እንዴት መስራት እንዳለባቸው ለመንገር አንሞክርም፤” ብለዋል ብሩክስ (Brooks)።

ንውፈር (Neufer) - በACPS የመካከለኛ ደረጃ (middle) ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ከመስክ-ጉዞው የሚገኙትን ጥቅሞች - የ‘Building Momentum’ን እንደየክፍሉ - የበጋ (Summer) ትምህርት ፕሮግራም አድርጎ አንዱ-አካል አድርገው-ጠርተውታል። እርሳቸውም እንዳሉት፤ ተማሪዎች ስለደህንነት-ጥበቃ መመሪያዎች - በተለያዩ መሣሪያዎች እና ቴክኖሎጂዎች በሚሰራበት ጊዜ መከተልን-እንዳለባቸው ተምረዋል። በተጨማሪም-ተሞክሮ አድርገው በስራ-ላይ ያዋሉት ትምህርት - ሌዘር መቁረጫ (laser cutting)፣ ብየዳ/welding፣ በኮምፒውተር የታገዘ ዲዛይን እና የእንጨት-ስራን ያካተተ-ነው። ንውፈር (Neufer) ሲናገሩ፤ ይህ የመስክ ጉዞ - ከቨርጅኒያ አርክቴክቸር እና የኮንስትራክሽን የስራ-መስክ ክለስተር ጋር በዲዛይንስ አሰራር እና ግንባታ ላይ ቀጥተኛ-የሆነ ግንኙነት ለማድረግ አገልግሏል። የመስክ ጉዞው (field trip)፣ ተማሪዎች የስራ-መስኮች መንገዶችን - ከ‘Career Clusters’ ዓላማ ያደረገ ከዲዛይን የኮርስ-ጥናቶች ጋር፣ ወደ የስራ-መስክ ግባቸው እንዲዘልቁ ለመፈተሽም-ረድቷቸዋል።

የ‘Building Momentum’s Innovation Academy’ ትኩረት የሚያደርገው፤ ከመማር ጋር የተጣመረ አቀራረብን - ሣይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግ፣ ሂሳብ እና ስነጥበባትን በክፍሎቹ ውስጥ በማካተት ላይ ያተኩራል። አዲስ የሆነ ግኝትን - በከትምህርት ቤት ውጪ (out-of-school)፣ ከትምህርት-ቤት በኋላ (after-school) እና በበጋ ፕሮግራሞች (summer programs) ውስጥ የሚሰጥ እና፣ የነገውን ችግር ለመፍታት ምን ማድረግ እንዳለባቸው መማለ ለሚፈልጉ ተማሪዎች - ለማገልገል-የተዘጋጀ ነው።

“ከእነዚህ ተሞክሮዎች ተማሪዎች የሚወስዱት በሕይወት-ዘመናቸው ሁሉ የሚጠቅማቸውን ችሎታዎች ሲሆን፣ በቀላሉ ወደ መማሪያ-ክፍላቸው እና ወደ የየዕለቱ ኑሮአቸው ለማስተላለፍ ይችላሉ፤” ብለዋል ንውፈር (Neufer)፤ “አስቸጋሪ-ሁኔታዎችን፣ ስራዎችን እና ችግሮችን ከተለዋዋጭነት ጋር በመሆን እና ከተወሰነ-አስተሳሰብ ወጣ ባለሁኔታ በማሰብ - ለመፍታትናና ለመወጣት - የሚያስተምረን ነው።”

## ACPS፣ አዲሷን የ‘NVJDCS’ ርዕሰ-መምህር ዶ/ር ጃሚላ ኤም. ማኒ (Dr. Jamila M. Mannie)ን - ተቀብሏል



የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ ዶ/ር ጃሚላ ኤም. ማኒ (Dr. Jamila M. Mannie)ን - እንደ የ‘Northern Virginia Juvenile Detention Center School (NVJDCS)’ - አዲስ ርዕሰ-መምህር አድርጎ እንኳን-ደህና መጡ ሲል ደስታ-ይሰማዋል። ይህ የዶ/ር ማኒ (Dr. Mannie) የስራ-ድራሻ የሚሆነው፤ በ ‘NVJDCS’ ውስጥ የትምህርት-ፕሮግራሙን መቆጣጠር እና ማስተዳደር ሲሆን — የተማሪን ትምህርታዊ-ተሞክሮን እንዴት-ማሳደግ እንደሚቻል መወሰን — ከማሰር/detention ጋር በውስጥ መደበኛ-አሰራሮች እና በስቴት እና ፌደራል ፖሊሲዎች እና ድንጋጌዎች

መሠረት ተገገር ሆኖ መስራትን እያረጋገጠ በሚሰራበት ጊዜ ማካሄድ ነው። በACPS ውስጥ፣ አዲሱን ስራዋን - በዲሴምበር (Dec.) 5 ቀን 2022 ላይ ጀምረዋል።

ዶ/ር ማኒ (Dr. Mannie) - በጣም-በቅርብ ጊዜ እንደ ርዕሰ መምህር እና ረዳት ርዕሰ መምህር ሆነው ከK-12 ለሆኑ ክፍሎች - በ'ፕሪንስ ጆርጅ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Prince George's County Public Schools (PGCPS)' ውስጥ፣ ከ11 ዓመታት በላይ አገልግለዋል። በ'PGCPS' ውስጥ በነበራቸው የስራ ጊዜ ወቅት፤ ዶ/ር ማኒ (Dr. Mannie)፤ በመረጃ-ላይ መሠረት ያደረገ፣ በፍትሃዊ-እኩልነት ላይ ያተኮረ እና ትብብራዊነት ያለው የትምህርት ቤት ባህልን፣ ለውስጣዊ-አመራርነት የመስራት-አቅም እና ጥንካሬዎችን በሚያስገኝ-ሁኔታ - የትምህርት አሰጣጥ ሠራተኞች - የዲስትሪክት ስልታዊ ግቦችን (district strategic goals) እንዲመቱ ወይም ከግቡ-በላይ እንዲሰሩ፤ በስራ-ላይ አውለዋል። በተጨማሪም፤ የባለብዙ-ደረጃዎች (multi-tiered)፣ የባለብዙ-የዲስፒሊናዊ ጣልቃ-ገብነት ፕሮግራምን በመቅረጽ፤ የቀለም-ትምህርትን፣ የማህበራዊ እና ባህሪያዊ ፍላጎቶችን ለሁሉ በትምህርት ቤት ለሚማሩ ተማሪዎች ምላሽ-እንዲሰጥ-ቀርጸዋል።

ዶ/ር ማኒ (Dr. Mannie) ከዚህ-ቀደም፤ በደርሃም የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Durham Public Schools) ውስጥ - የተለየ-ችሎታ ላላቸው ልጆች የፕሮግራም ዳይሬክተር በመሆን ያገለገሉ እና፣ እንደ የልዩ ትምህርት (special education) የትምህርት አሰጣጥ ባለሞያ-ሆነው ለPGCPS ሰርተዋል። በ'Fairfax County Juvenile Detention Center' ውስጥ፤ ሁሉን-የማዳረስ ካውንስለር ሆነው የነበረ እና በፌርፋክስ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Fairfax County Public Schools) ውስጥም እንደ የልዩ ትምህርት (special education) አስተማሪ/ረዳት ርዕሰ መምህር ሆነው አገልግለው-ነበር

"የተማሪ አገልግሎቶች እና ፍትሃዊነት-እኩልነት (Student Services and Equity) መምሪያ - ዶ/ር ጀሚላ ማኒ (Dr. Jamila Mannie)ን እንደ አዲስ ርዕሰ መምህር አድርጎ - ለ'Northern Virginia Juvenile Detention Center educational program' መቀበሉ አስደስቶታል፤" ብለዋል የACPS የፍትሃዊ-እኩልነት & አማራጭ-ፕሮግራሞች ዋና ዳይሬክተር የሆኑት - ኬነትራ ኤን. ውድ (Kennetra N. Wood)። "ዶ/ር ማኒ (Dr. Mannie) - ለሁለቱም ለመጀመሪያ ደረጃ እና ለሁለተኛ-ደረጃዎች ትምህርታዊ-ተሞክሮዎችን ሃብት-የሚያጎናጽፉ፣ እና ለተማሪ ትምህርት እና ስኬታማነት - የጋለ-ስሜትን በማሳየት የሚያቀርቡ-ናቸው። ዶ/ር ማኒ (Dr. Mannie) ወደ 'NJVDCS' የሚያመጡት ልበ-ሙሉነት እና ልምድ - የማህበራዊ፣ ስሜታዊነት እና የተማሪዎቻችንን ትምህርታዊ ፍላጎቶቻቸውን በመደገፍ-የሚቀጥል እንደሚሆን፣ እንዲሁም ከK-12 ትምህርታዊ ስርዓትን ባለፈ-ሁኔታ በተማሪዎች የሽግግር-ፍላጎቶች ላይ ትኩረት ማድረጉን እንደሚቀጥል፤ ሙሉ ዕምነት አለኝ።"

ዶ/ር ማኒ (Dr. Mannie) - የባችለውር ዲግሪያቸውን በ'Human Sciences' በቤተሰብ ግንኙነቶች እና የልጅነት ዕድገት ላይ - ከኖርዝ ካሮላይና ማዕከላዊ ዩኒቨርስቲ (North Carolina Central University) አግኝተዋል። ማስተርሳቸውን በልዩ ትምህርት (special education): በመማር እና በስሜታዊ ጉዳተኝነት ከPreK-21፣ ከ ጆርጅ ሜሰን ዩኒቨርስቲ (George Mason University) ያገኙ እና የፖስት-ግራጁዌት የሙያ-ስልጠናቸውን - በአስተዳደር እና ቁጥጥር ከPreK-12፣ ከቨርጂኒያ ዩኒቨርስቲ አግኝተዋል። የዶክትሬት ዲግሪ ትምህርታቸውን፣ በትምህርታዊ አስተዳደር እና አመራርነት፣ ከዋልደን ዩኒቨርስቲ (Walden University) ያገኙ እና የአስተዳደር ሰርተፊኬቶችን (I እና II) - ከ'Maryland State Department of Education' ይዘዋል።

# የ‘ACHS’ የምግብ-ስራ ተማሪዎች፤ ለአሌክሳንድርያ የስኮላርሽፕ የገንዘብ-እርዳታ፤ ገንዘብ አሰባስበዋል



የ‘The dreams of budding’ ሼፎች፤ በአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) ውስጥ - እንደ የምግብ-አሰራር ስነጥባት ተማሪዎችን እውቅና-በሰጠበት ጊዜ፤ የጂንጀርብሬድ ቤቶች (gingerbread houses)ን በመስራት፤ ለThe Scholarship Fund of Alexandria (SFA) የገንዘብ-ማሰባሰብን አድርጓል። የተማሪዎች ቡድኖች፤ በቅርቡ ባሳዩት የምግብ-አሰራር ችሎታቸው ላይ - በቀጥታ-በተሰራጨው የfor Fox 5 ላይ፣ አስደሳች-የሆኑ፣ እና በእውነት-ጣፋጭ-የሆኑ የጂንጀር-ብሬድ (gingerbread) ፈጠራዎቻቸውን አሳይተዋል።

የ‘winter wonderland’ ገጽታ/theme ያለውን፤ እንደ አንዱ የጂንጀር-ብሬድ ቤቶቻቸው (gingerbread houses) የሃሳብ-ማነሻሻ አድርገው ተጠቅመውታል። የቀለጡ የ‘Jolly Ranchers’ እንደ የበረዶ-ፍንጣቂ (snowflake) ቅርጽ-ያለው መስኮትን ለመስራት እና የ‘gummy bears’ በመንሸራተቻው/sled ውጪ እንዲቀመጥ ረድተው-ነበር። ሌላም-ጥሩ የሰሩ መኖራቸው ሳይካድ፤ ሌላ ቡድን - የጂንጀር-ብሬድ ቤቱ (gingerbread house)ን በስሱ የተሰነጣጠቁ የስንዴ ሴሊያል (shredded wheat cereal) እና በኸርሺ ኪስስ (Hershey’s Kisses) - የበረዶ ጣሪያውን ለመስራት ተጠቅመዋል። ሼፍ ክሬግ ሹመርማን (Chef Craig Scheuerman) - የACHS የምግብ-አሰራር የስነ-ጥበታት አስተማሪ የሆኑት - ሌላ የራሳቸው የሆነውን የ“Caps” ማስተርፒሶች/masterpiecesን - ለዋሽንግተን ዲሲ ካፒታል አይስ ሃኪ ደጋፊዎች (ice hockey fans) ለእነርሱ ተለይቶ የተሰራውን፣ ከዚህ-ቀደም $150 ለእነዚህ አንድ ቁንጆ-የሆኑ የጂንጀርብሬ ቤቶች (gingerbread homes) የገንዘብ-ማሰባሰቢያ አስገኝቶ-ነበር።



“ተማሪዎቹ ያላቸው ፈጠራዊ-ችሎታ የሚደነቅ-ነው፣” በኩራት ሹመርማን (Scheuerman) ሲናገሩ፤ በየዓመቱ እየጨመሩ ሲመጡ፣ ተማሪዎች እራሳቸውን የሚያስደንቃቸውን በፊት-የሰሩትን የሚያስንቅ-ስራን ይሰራሉ። የጂንጀር-ብሬድ ቤቶቹ (The gingerbread houses) ለ‘SFA’ የገንዘብ-ማሰባሰቢያ አንዱ አካል ሆኖ - በምግብ-ስራ ስኮላርሽፕን ለማግኘት ለሚሹ ሼፎች እንዲሆን፤ በጨረታ የቀረበ ወይም የተሸጡ ናቸው። ተማሪው በሚወስዱት በማንኛውም የስራ-መስክ በየትኛውም-ቦታ ብበስራ-ላይ ሊውል የሚችል፤ ለአገኙት የቡድን-ግንባታ የአሰራር ችሎታ ምስጋና-ይግባውና፤ ሁሉም በጂንጀር-ብሬድ (gingerbread) ግንባታ ላይ የተሰተፉ ሁሉ - አሸናፊዎች ሆነው ሄደዋል - ብለው ሹመርማን (Scheuerman) አምነዋል። እርሱም-እንዳለው፤ ተማሪዎች በክፍል-ውስጥ የተማሩት ትምህርት በሕይወት ላይ ለሚጠቀሙት ችሎታዎች ወሳኝ-ሆኖላቸዋል… “ምግብ-መስራት ግሩም-የሆነ ነገር ነው በእውነት ለመስራት አስደሳች ነው።”

“በእውነት የቡድናችን የጋራ-ጥረት ነው እዚህ ያደረሰን፣ ሁላችንም በእውነት ጠንክረን-ሰርተናል” ብላለች ሳራ ሲንቶ (Sarah Shinto) የACHS senior።

# ቀኑን-አስታውሱ፤ እዳትረሱት: የ2023 የአሌክሳንድርያ ከተማ የሣይንስ ትዕይንት - የሚዳኙ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች (Volunteer)



የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ቤተሰብ እና ማህበረሰብ አባላቶች፤ በ2023 የACPS የሣይንስ እና የኢንጂነሪንግ ትዕይንት ላይ - የጊዜ-ሰሌዳው ለሐሙስ ጃንዋሪ (Jan.) 26 ቀን 2023 - በAlexandria City High School (ACHS) - King Street Campus (3330 King Street) ውስጥ ለተያዘለት፤ እንደ ዳኞች ሆናችሁ እንድታገለግሉ ይጋብዛል። በዚህ-ዓመት ወደ በአካል-ተገኝቶ (in-person̈) ዝግጅት በመመለሳችን - ደስተኞች ነን።

የምሽት የጊዜ-ሰሌዳ የተያዘላቸው ዝግጅቶች የሚከተሉት ናቸው:

- ከ5-5:30 p.m. — የዳኞች ምዝገባ እና እራት።
- ከ5:30-6 p.m. — ዳኞችን ማስተዋወቂያ/Judges' orientation (እራት እና ምዝገባው-ይቀጥላል)።
- ከ6-8 p.m. – ፕሮጀክቶችን መዳኘት (Judging of Projects).
- ከ8-9 p.m. — የዳኞች የስራ ክፍለ-ጊዜ/Judges work session እና አስተያየቶችን መስጫ/award recommendations (ይህ ዳኞች እንደጨረሱ -አንዱ ከሌላው ተከትሉ የሚካሄድ ነው)።

ከእኛ ጋር አብሮ ለመካፈል እና እንደ ዳኛ ሆኖ ለማገልገል መገኘት-የምትችሉ ከሆነ፤ ከክረምት-የዕረፍት ጊዜው በኋላ በሣይንስ ትዕይንት (science fair) ድህረ-ገጽ ላይ እና በ'ACPS Express' ላይ የመመዝገቢያ (sign-up) ቅጽ እንዲገኝ-የሚደረግ ይሆናል።

በሣይንስ ትዕይንቱ ላይ፣ ስብጥር-ያላቸው ከ6-12ኛ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ የታዳጊ-ልጆች ቡድንን ማግኘት ትችላላችሁ። ይህም የሚያካትተው፤ ጀማሪ ተመራማማሪዎች የሆኑ ተማሪዎችን፣ እንዲሁም ልምድ-ያላቸውን የሣይንስ ትዕይንት ተሳታፊዎችንም ያካተታል። ከሣይንስ ትዕይንቱ፣ በጣም ትውስታን የሚፈጥር እና መንፈስን-የሚያነሳሳው ነገር - ከዳኞች ጋር ያላቸው የእርስ-በርስ ግንኙነቶች፣ መሆናቸውን ተማሪዎች አብዛኛውን-ጊዜ ሪፖርት ያደርጋሉ።

መጥፎ-የአየር-ሁኔታ ከተፈጠር፤ ሌላ ተቀያሩ ቀን - ለጃንዋሪ (Jan.) 31 ቀን 2023 - የጊዜ-ሰሌዳ የሚያዝ-ይሆናል።

## የማህበረሰብ ስብሰባ - ማጠቃለያ፣ ስለ 1703 N. Beauregard St. ህንፃ ለመወያየት



የካፒታል ፕሮግራሞች፣ ዕቅድ-ማውጫ እና ዲዛይን ቢሮ (The Office of Capital Programs, Planning and Design) - የመጀመሪያው የሆነውን - ስለ በ703 N. Beauregard St. ላይ በቅርቡ-ስለተገዛው ንብረት በተመለከተ፣ የርቀት (virtual) የማህበረሰብ ስብሰባን፣ ሰኞ ዲሴምበር (Dec.) 5 ቀን 2022 ላይ አድርጎ-ነበር። ለጆርጅ ሜሰን (George Mason) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ለኮራ ኬሊ (Cora Kelly) ትምህርት ቤት ለሂሳብ፣ ሳይንስ ቴክኖሎጂ - ለሁለቱም፤ በዚህ በዘመናዊነት ማሻሻያ ጊዚው ወቅት፣ ህንፃውን እንደ-ጊዜያዊ መሸጋገሪያ ቦታ ሆኖ ጥቅም-ላይ ይውላል። የፕሮጀክት ቡድኑ፤ የሚጠበቀውን የጊዜ-አቀማመጥ ያቀረቡ እና የማህበረሰቡን ጥያቄዎች ላይ - ስለ በጀት፣ የተማሪ መጓጓዣ እና የካምፓስ ሎጂስቲኮችን ጨምሮ፤ ምላሽ-ሰጥቶ ነበር። የዲዛይን የስራ-ሂደት ቀጣይነት-ያለው፣ እና ተጨማሪ ስብሰባዎች በመጪው ወራቶች ውስጥ - የማህበረሰቡን አስተያየት ለመሰብሰብ እንዲረዳ የጊዜ-ሰሌዳ የሚያዝለት ይሆናል።

የስብሰባውን አቀራረብ (meeting presentation) ለመመልከት፤ የ[ካፒታል ፕሮግራሞች፣ ዕቅድ-ማውጫ እና ዲዛይን ቢሮ (The Office of Capital Programs, Planning and Design)] ድህረ-ገጽን ጎብኙ። በተጨማሪም፤ የወርሃዊው የ[ACPS Capital Improvement Program newsletter] አባል-ሆኖ መመዝገብ (subscribe ማድረግ) - በቅርብ-ጊዜ በተሰራው የፕሮጀክት ማበልጸጊያዎች ላይ እና መረጃዎች አዲስና-ማስተካከያ ማግኘታችሁን የሚያረጋግጥ-ይሆናል።

## ስለ የክረምት የአየር-ጠባይ ሁኔታዎች (Winter Weather Communications) መረጃዎችን ለማግኘት፤ የ‘ParentSquare’ አፕ/App - ዳውንሎድ አድርጉ




ወደ ክረምት ወራቶች እየገባን ባለንበት ጊዜ፣ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (ACPS) - በአካል ተገኝቶ (In-Person) ትምህርት አሰጣጥ ሊካሄድባችው በማይቻልባቸው ቀናቶች ላይ ዕቅድ አቅዷል። ዕቅዳችንም የሚያካትተው፤ የክረምት የአየር-ጠባይ (winter weather) ሁኔታዎች በሚከሰቱ ጊዜ፤ የማስታወቂያ ሂደቶችን እና የመማር ሂደት መቀጠልን አካትቶ-የያዘ ነው። ግባችን፣ ማንኛውም የወደፊት ትምህርት ቤቶች መዘጋት በሚያስፈልጋቸው ቀናቶችን ጠብቀን እያለን፣ የመማር ሂደቱ እንዲቀጥል ማገዝ ነው። በክረምት የአየር ጠባይ ምክንያት - የተዘጋው የመጀመሪያው የትምህርት ቀን በርቀት (virtual) መደበኛ-ባልሆነ መንገድ (asynchronous) የሚሰጥ የትምህርት-አሰጣጥ ሊሆን እንደሚችል፤ ይህም ተማሪዎች አንድ-ዓይነት የሆነውን ማቴሪያል መማር የሚያስችላቸው ሲሆን፣ ነገር ግን - በተለየ ጊዜያቶች እና ቦታዎች ላይ - በቀጥታ-ከሚሰጥ የትምህርት አሰጣጥ ውጪ በሆኑ መልኩ የሚሰጥበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል - ቤተሰቦች፣ ዝግጅት-ማድረግ ያስፈልጋቸዋል። ትምህርት ቤቶች ከአንድ-ቀን በላይ መዘጋት-የሚያስፈልጋቸው ከሆነ፤ ተጨማሪ መረጃዎችን የምናጋራችሁ

ይሆናል። ተማሪዎች መደበኛ-ባልሆነ መንገድ (asynchronous) ትምህርት በርቀት (virtual) መማር ውስጥ በእያንዳንዱ የትምህርት ቤት ደረጃ ውስጥ እንዴት መካፈል እንደሚችሉ ተጨማሪ-ዝርዝሮችን ለማግኘት፤ እባካችሁ የእኛን የክረምት (winter) የአየር-ጠባይ ግንኙነቶች ድህረ-ገጻችንን ጎብኙ።

## የክረምት-ወቅት የአየር-ጠባይ ሁኔታዎችን - መገምገም

የክረምት የአየር-ጠባይ (winter weather) በሚከሰት-ጊዜ፤ — እንደ በረዶ፣ አይስ/ice ወይም ከመጠን በላይ ቀዝቃዛ የአየር-ጠባይ— በሚከሰት-ጊዜ፣ እና አውቶቡሶችም ወደ ትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት በደህንነት የመንቀሳቀስ ሁኔታ ሳይኖራቸው ሲቀር፤ ACPS የትምህርት ቤት ህንፃዎችን መዝጋት የሚያስፈልገው እና የርቀት (Virtual) የትምህርት አሰጣጥም በእነዚህ ሁኔታዎች ወቅት በመኖሪያ ቤት ውስጥ ይካሄዳል። በተጨማሪም፤ ወደ ትምህርት ቤት በእግራቸው ለሚመጡ - ወደ ትምህርት ቤት መምጣቱ ደህንነታቸው-ሊጠብቅ የማይችል ከሆነ፤ ወይም ለሠራተኞች ለመጓጓዝ አደገኛ ከሆነ፤ በመኖሪያ-ቤት ውስጥ የሚሰጥ የርቀት (Virtual) የትምህርት አሰጣጥ ለማካሄድ ውሳኔ ይደረግ-ይሆናል። በክረምት የአየር-ጠባይ (winter weather) ሁኔታዎች ወቅት ትምህርት ቤቶችን ለመዝጋት ስንመለከት፣ የተማሪዎቻችን እና የሠራተኞቻችን የደህንነት ሁኔታ፣ የእኛ ቁጥር አንድ ቅድሚያ የምንሰጠው-ጉዳይ ነው። ስለ መንገድ ሁኔታዎች ከአሌክሳንድርያ ከተማ የአስቸኳይ ጊዜ ቁጥጥር ሰራተኞች ጋር በመሆን፤ የመንገዶችን ሁኔታ እና የሕዝብ በእግር-መሄጃች ሁኔታዎቻቸውን ለመገምገም፤ የትምህርት ቤት ሠራተኞችም - የአውቶቡስ የመጓጓዣ መስመሮችን ደህንነት፣ የACPS የመኪና ማቆሚያዎች እና የአውቶቡስ መስመሮች በተመለከተ ግምገማ-በማድረግ ላይ፣ በጥምረት እንሰራለን።

ቤተሰቦች እና ሠራተኞች ቀደም-በልው ዝግጅቶችን ማድረግ እንዳለባቸው በማሰብ፤ ACPS፣ የትምህርት ቤት መዘጋት ውሳኔዎችን ከክረምት የአየር-ጠባይ ሁኔታው ከሚኖርበት ቀን በፊት ባለው ምሽት ለማሳወቅ ሙከራ ያደርጋል። ሆኖም ግን፤ በአየር-ጠባይ ትንበያ ዙሪያ በሚኖሩ በርካታ የማይታወቁ-ነገሮች ምክንያት፤ የመጨረሻውን የጠዋት ትንበያውን እና የመንገድ ሁኔታዎች አዲስና ማሻሻያ (update)ን ከአሌክሳንድርያ ከተማ የአስቸኳይ-ጊዜ ቁጥጥር (City of Alexandria emergency management) ሠራተኞች እስከሚሰጠን እንጠብቃለን። ሊፈጠር በሚችለው የአየር-ጠባይ ሁኔታ ቀድሞ ባለው ምሽት ውሳኔውን ለማሳወቅ በማንችል ጊዜ፤ ጠቅላይ ስራ አስኪያጁ - የትምህርት ቤት ህንፃዎች መዘጋት አለመዘጋት ውሳኔውን እና በመኖሪያ ቤት የርቀት (Virtual) የትምህርት አሰጣጥ ለተማሪዎች መሰጠቱን፣ በግምት ወደ 5:00 a.m. ላይ ያሳውቃሉ። በየትኛውም ሁኔታ ቢሆን፤ በACPS ድህረ-ገጽ እና 'ParentSquare' አማካኝነት፤ ቤተሰቦች እና ሠራተኞች መደበኛ አዲስና ማሻሻያዎች (updates)ን ያገኛሉ።

## ለ'በመኖሪያ-ቤት የርቀት (Virtual) የትምህርት አሰጣጥ' መዘጋጀት

በክረምት የአየር-ጠባይ ወቅት (winter weather season) እንደመደበኛ ልምድ-ሆኖ መደረግ ያለበት፤ በእያንዳንዱ የትምህርት ቀን መጨረሻ ላይ፣ ተማሪዎች ኮምፒውተሮቻቸውን/ዲቫይሶቻቸውን (computers/devices) እና የመማሪያ ቁሳቁሶቻቸውን ወደ መኖሪያ ቤታቸው እንዲወስዱ በእጅጉ-ይመከራሉ። ይህ፤ በመጥፎ የአየር-ጠባይ (inclement weather) ምክንያት ትምህርት ቤቶች መዘጋት ሲኖርባቸው፤ ተማሪዎች የሚያስፈልጓቸው ቁሳቁሶች በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ መኖሩን ለማረጋገጥ ነው። የመጀመሪያው የርቀት (virtual) መማር ቀን፣ በመደበኛ-ባልሆነ የትምህርት አሰጣጥ (asynchronous) በኦንላይን-የሚከናወን ሲሆን፤ ይህም፣ ተማሪዎች አንድ-ዓይነት ይዘቶች/materialን ለመማር፣ ነገር ግን - የቀጥታ (live) የትምህርት አሰጣጥ ሳይኖር - በተለያየ ጊዜያቶች እና ቦታዎች ላይ በመሆን፣ በክረምት የአየር-ጠባይ/winter weather የግንኙነቶች ድህረ-ገጻችን ላይ በተገለጸው-መሠረት እንዲማሩ የሚያደርጋቸው ነው። ትምህርት ቤቱ በአካል ተገኝቶ (In-Person) ትምህርት ለመስጠት ከአንድ ቀን-በላይ የሚዘጋ ከሆነ፣ ስለ ርቀት (virtual) ትምህርት አቀማመጥ - ለቀጣዮቹ ቀናቶች የሚኖረውን አዲስና-ማሻሻያ (update)፣ ቤተሰቦችን የሚያገኙ-ይሆናል።

## ከቤተሰቦች እና ሠራተኞች ጋር የሚደረግ ግንኙነት

ከክረምት የአየር-ጠባይ ጋር በተያያዘ ትምህርት ቤት በሚዘጋ-ጊዜ፤ ቤተሰቦች እና ሠራተኞች - በኢሜል እና በ'ParentSquare' አማካኝነት፣ ማስታወቂያን ያገኛሉ። ይህ መረጃ፤ መደበኛ የክንውን-እንቅስቃሲው እስከሚቀጥል ድረስ - እንደተለጠፈ (post እንደተደረገ) ይቀጥላል። በተጨማሪም፤ የACPS ድህረ-ገጽ፣ አጣዳፊ መስመር (hotline) እና የማህበራዊ ሚዲያ (social media) አውታሮች፤ ተገቢ-የሆነውን የመረጃ ማንቂያ (alert) የሚያካትቱ፤ እና 'ACPS'ም፣ ከክረምት የአየር-ጠባይ ጋር የተያያዙ መዘጋቶችን በአካባቢው የዜና ማሰራጫዎች እና በማህበረሰብ አጋርነት-አማካኝነት የከትምህርት በኋላ የትምህርት-አሰጣጥን በሚሰጡ እና/ወይ በልጅ-እንክብካቤ (Child

Care) በኩል፣ መረጃውን ያጋራል። የACPS ትምህርት ቤቶች ዝግ-ሲሆኑ፣ የከትምህርት በኋላ (after-school) እና የልጅ-እንክብካቤ ሰጪዎች (childcare providers) ጋር ስለ የስራ-ክንውናቸው - አንዳንድ አገልግሎት-ሰጪዎች ከተለመደው የትምህርት ቤት ቦታ ውጪ አገልግሎቶችን ሊሰጥ ስለሚችሉ፣ ከእነርሱ-ጋር በቀጥታ ያለውን-ሁኔታ እንዲያረጋግጡ ለቤተሰቦች እናበረታታለን። ሁሉም የ'ACPS' ሠራተኛ እና ቤተሰቦች የከረትም የአየር-ጠባይ ማስታወቂያዎችን እና አዲስና ማሻሻያዎች (updates) ወዲያውኑ ከትምህርት ቤቱ ክፍሉ/division እንደተላኩ ለማግኘት እንዲችሉ የ'ParentSquare አፕ/app'ን ዳውንሎድ እንዲያደርጉ እንመክራለን።

## የዲሴምበር (Dec.) 15 ቀን 2022 - የትምህርት ቤት ቦርድ አጀንዳ



በመደበኛነት የጊዜ-ሰሌዳ የተያዘለት የሚቀጥለው የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ - ዲሴምበር (Dec.) 15 ቀን 2022 ላይ ነው፣ እና ከቅድመ-ልጅነት ማዕከል (Early Childhood Center) እና ከ'new School Board vignette' የሚቀርበውን የ"Simply the Best" አቀራረብ/presentation - ስለ 2025 ፍትሃዊ-እኩልነት ለሁሉም (Equity For All) - ዋናው ዕቅድ (Strategic Plan) ያለውን ግንዛቤ ለማጠንከር እንዲረዳ፣ የሚያካትት-ይሆናል። በተጨማሪም፣ የትምህርት ቤት ቦርድ - የ'ESSER III' የገንዘብ-እርዳታዎችን አጠቃቀም ላይ የ'Public Hearing'ንም የሚያደርግ-ይሆናል። የመናገር-ጥያቄን — በአካል-ቀርቦ (in person)፣ በዙም(Zoom) አማካኝነት ወይም በጽሁፍ-አስተያየትን የማቅረብ-ጥያቄ — እስከ ሮብ ዲሴምበር (Dec.) 14 ቀን 2022 ድረስ - የ'Public Hearing' መመዝገቢያ/sign-up ቅጽን በመጠቀም መግባት-አለበት።

የዚህ ስብሰባ አጀንዳ የሚከተሉትን ጉዳዮች ያካተተ ይሆናል:

- የ'Capital Improvement Planning (CIP)'ን የማስፈጸሚያ በጀት
- የደህንነት-ጥበቃ የዳሰሳ-ጥናት እና የ'SLEP focus group' ውጤቶች
- የACPS የሕጋዊነት አጀንዳ
- የ'ESSER III' የገንዘብ-እርዳታዎች ላይ የተደረገ አዲስና ማሻሻያ (Update)

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፣ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፣ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ መጎብኘት ትችላላችሁ።

# በዲሴምበር (Dec.) 1 ቀን 2022 - COVID-19 የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት-ደረጃ




እስከ ዲሴምበር (Dec.) 1 ቀን 2022 - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - ዝቅተኛ/low ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤  በየ100,000 ሰዎች፣ 106.6 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤ [Alexandria COVID-19 dashboard] ጎብኙ።

የመረጃ-ስብስቡ (data)፤ በመጨረሻ-እንዲስተካከል የተደረገው በዲሴምበር (Dec.) 1 ቀን 2022 ላይ እንደሆነ፣ እባካችሁ አስታውሱ። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት (Centers for Disease Control and Prevention)፤ በሦስት ሜትሪክስ (three metrics) ጥምሮች ውስጥ - የCOVID-19 የማህበረሰብ የደረጃ-መጠንን ለመወሰን ተመልክቷል: አዲስ የCOVID-19 ታማሚ ሆነው የተመረመሩበትን በ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ፤ ገብተው-የተኙ በCOVID-19 ታካሚዎች የተያዙ አልጋዎች - በእያንዳንዱ የCOVID-19 በሽተኛ-ቁጥር፤ እና አጠቅላይ አዲስ የCOVID-19 ታማሚዎችን በየ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ ተመልክቷል።